† #ዘማሪነት_እና_የመዘምራን_ሕይወት†

#ዘማሪነት

ከእግዚአብሔር የሚሰጥ ልዩ የአገልግሎት ጸጋ ነው።

የትምህርተ ሃይማኖት፣ የቅዱሳት መጻሕፍት በሳል ዕውቀት እንዲሁም ክርስቲያናዊ ሕይወትን የሚጠይቅ አገልግሎት ነው።

በልምድ ብቻ የሚገኝ ሙያ አይደለም።

ለአገልግሎት ጥሪ ምላሽ የሚሰጥበት የትህትና ሕይወት ነው።

ሙያዊ ችሎታን ለእይታ የሚያቀርቡበት የሙያ ዘርፍ አይደለም።

እንደ ዩሐንስ መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ፣ ወደ እግዚአብሔር ቅረቡ፣ በሥጋ ወደሙ ራሳችሁን አዘጋጁ፣ ከቂም ከበቀል ራሳችሁን አንጹ...በማለት ቃለ እግዚአብሔርን በዜማ የምናስተምርበት ነው። ስለዚህ ዘማሪያን መምህራን ናቸው።

ምድራዊ መላእክት መሆን ነው።

➢ "እግዚአብሔርን አመስግኑት መላዕክቱ ሁሉ እግዚአብሔርን አመስግኑ"(መዝ ፻፶፰፥፪)

➢ "ሰማዕታትን በደም፣ ጻድቃን በገዳም፣ ሐዋርያትን በአጽናፍ ዓለም፣ መላዕክትን በምስጋና በአርያም" እንዲል።(አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ)

#የመዘምራን_ሕይወት

መዘምራን የምስጋና መስዋዕት አቅራቢዎች፣ በምድር የመላእክት አገልግሎት ፈጻሚዎች እና አስተማሪዎች ናቸው። ለእግዚአብሔር የሚቀርብ መስዋዕት መልካም ንጹህ እንደሆነ ሁሉ መዝሙሩም መመረጥና ከቤተ-ክርስቲያን ሥርዓትና ትውፊት አንጻር መመርመር ይኖርበታል። (ዘሌ ፳፫፡፲፪)

መዝሙሩም ብቻ ሳይሆን መስዋዕት አቅራቢዎችም ራሳቸው ለእግዚአብሔር የተቀደሱ ሊሆኑ ይገባል (ሮሜ ፲፪፡፲፪)። አለበለዚያ ግን የቃየል መስዋዕት ሆኖ ይቀራል (መዝ ፻፲፭፡፳)

የመዘምራን አለባበስ ሥርዓት የጠበቀ መሆን ይገባዋል።ይኽም የልብስን ብቻ ሳይሆን የአቋቋምንና የልብ /የውስጥ/ ስሜትንም ሁኔታ ያጠቃልላል። የሥራ ልብስ እንዳለ ሁሉ ለመዝሙርም የራሱ ልብስ ይኖረዋል። "ሴቶች በሚገባ ልብስ በእፍረትና እራሳቸውን ከመግዛት ጋር ሰውነታቸውን ይሸልሙ እግዚአብሔርን እንፈራለን በሚሉ ሴቶች ደግሞ መልካም ከማድረግ እንጂ በሹርባ በወርቅ ወይም በዕንቁ ዋጋ እጅግ በከበረ ልብስ አይሸለም "(፩ጢሞ ፪፥፱-፲)

ከአለባበስ ሥርዓት መውጣት ከመንፈሳውያን የማይጠበቅ ነው። ለአለባበሳችን መነሻ የሆኑን ልክ እንደ መዝሙሩ ሁሉ ቅዱሳን መላእክት ናቸው። "ሱራፌልም ከእርሱ በላይ ቆመው ነበር ለእያንዳንዱም ክንፍ ነበረው በሁለቱም ክንፋቸው ፊታቸውን ይሸፍኑ ነበር...።"(ኢሳ ፮፡፩) ከዚህ የምንረዳው በፍርሃት ሆነን በእግዚአብሔር ፊት እንዳለን በማሰብና በመሸፋፈን መዘመር እንዳለብን ነው። ዛሬ የካህናቱ አለባበስ የመዘምራኑ ጥንግ ድርብ ከላይ እሰከታቸ ያለው ሁሉ ከመላእክት የክንፍ ሁኔታ ጋር ምስጢር ያለው ነው። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ "ወንደሞች ሆይ ከእኛ እንደተቀበለው ወግ ሳይሆን ያለሥርዓት ከሚሄድ ወንድም ሁሉ ትለዩ ዘንድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እናዛችኋለን " እንዳለ ።(፪ኛተሰሎ ፫-፮)

#ከአገልጋይ_መዘምራን_ምን_ይጠበቃል

በጸሎት መትጋት፦መዝሙር ከመዘመሩ በፊትም ሆነ ከተዘመረ በኋላ ጸሎት ያስፈልጋል መዘምራን የሆነው በራሳችን ጥበብና ድምፅ ማማር አለመሆኑን ተገንዝበን ለመረጠንና በቦታው እንድናገለግል ላደረገን አምላክ ምስጋና በማቅረብ ለወደፊቱም በቸርነቱ እንዲጠብቀን ዘወትር የጸሎት ሰዎች መሆን ይገባናል ። የበለዓምን አህያ ፣ የቢታንያን ደንጋዮች ያናገረ፣ የሆሣዕናን አህያ የመረጠ እግዚአብሔር ዛሬም ከምንም ቦታ ዘማሪያንን

ሊያስነሳ ይችላልና ተመርጠን እንዳንጣል ጸሎት ያስፈልጋል ። ለመዝሙር ክብር በመስጠት ልክ እንደ ልበ አምላክ ቅዱስ ዳዊት ከልብ መዘመር እንጂ እንደ ሜሊኮል መታበይ አይገባም ። (፪ኛ ሳሙ ፮፡፩ -ፍ.ም)

በማን ፊት እንደቆሙ ማወቅ፦ንጹሃ ባሕርይ የሆነ አምላክ ዘንድ በምን መልኩ መቅረብ እንዳለብን ቤተ-ክርስትያን በሰፊው ታስተምረናለች። መዝሙር እግዚአብሔር የሚመሰገንበት የእርሱ የሆነ ሁሉ የሚዘከርበት በመሆኑ መዝሙር በሚዘመርበት ቦታ ሁሉ እግዚአብሔር መኖሩን ባለመዘንጋት መዘምራን ሲዘምሩ በእግዚአብሔር ፊት እንደቆሙ በማሰብ እንጂ የሚያውቁትንና የሚያደንቀቸውን ሰው ፍለጋ ዓይንን በማማተር መሆን የለበትም። ይህ እራሱ መታበይ ነውና የአገልግሎቱ ዋጋም በምድር እንዲቀር ያደርጋል።

ያወቁትን ለሌላው ማሳወቅ (ማስተማር)፦ በቤተ ክርስቲያናችን የምናገኛቸውን ማናቸውንም ነገሮች እስከ ዘመናችን የደረሱት በትውፊት አንዱ ለአንዱ እየሰጠ ፣እያስተላለፈ፣ እየተቀበለ መሆኑ አይካድም ። በአባቶችና በትውልድ መካከል መለያየት እንዳይኖር ያወቁትን እያሳወቁ መጓዝ ይገባል ።

እራስን ለእግዚአብሔር ማስገዛት፦ እግዚአብሔርም ወደ አቤልና ወደ መስዋዕቱ ተመለከተ ንጹህ መስዋዕት አቅርቧልና እግዚአብሔር መስዋዕቱን ተቀበለ።(ዘፍ ፬፥፬) እግዚአብሔር ከሚቀርበው መዝሙር በፊት ዘማሪውን ይመለከታል ስለዚህ ዘማሪው በንጽህና ሊቀርብ ይገባዋል። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም "ወንድሞች ሆይ ሰውነታችሁን ቅዱስ እና ንጹህ መስዋዕት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ በእግዚአብሔር ርህራሄ እለምናችኋለሁ" ሲል ይመክረናል። በኃጢያት የረከሰ ከንፈር በንስሐ፣ በሥጋ ወደሙ መቀደስ አለበት።

ጸጋን ማወቅ፦የጸጋ ስጦታ ልዩ ልዩ ነውና። ሰባኪያነ ወንጌል ስብከትን፤ መዘምራን መዝሙሩን ፣በገና ደርዳሩዎች በገናቸውን ፣ መሰንቆ መቺዎች መሰንቋቸውን.... እየደረደሩ እና እየገዘገዙ መዝሙርን ሊያቀርቡ ይገባል።

ጥንቃቄ ማድረግ፦ የመዘምራን አገልግሎት ለዓይን የሚታይ እንደመሆኑ መጠን ለተመላካቾች፣ ለአድማጮች፣ በመዝሙራችን የምናስተላልፈውን እኛ በተግባር እየፈጸምን ማሳየት ይኖርብናል። "ትህትናን እንደ ልብስ ታጠቁ።"(፩ኛጴጥ.፭፥፭) "ስለምናገለግለው ለዚህ ለጋስ ስጦታ ማንም እንዳይነቅፈን እንጠነቀቃለን።"(፪ኛ ቆሮ ፰ ፥፳)

ቸልተኛ አለመሆን፦"የእግዚአብሔርን አገልግሎት በቸልታ የሚያደርግ ሁሉ እርጉም ይሁን።"እንዲል መጽሐፍ(ኤር.፵፰፥፲ ዮሐ.፲፬፥፳)

መዝሙሩን በቃል መያዝ፦ አድማጮች የመዝሙሩን መልእክት አእምሮአቸው ሳይረበሽ ለመረዳትና ለመያዝ እንዲችሉ።

ለመዝሙር ሥርዓት መገዛት፦ ዘማርያን ቤተ-ክርስቲያናችን በየጊዜው ለምታወጣው ደንብና መመሪያ መገዛት አለባቸው። መዝሙር የቤተ ክርስቲያን ሀብት እንደመሆኑ መጠን በመዋቅር ደረጃ ቤተ-ክርስቲያኒቱ የመዝሙር ክፍል በሥሯ ይዛ በሥርዓትም እንዲመራ መመሪያ አውጥታለች። መዘምራን ለዚህ መመሪያ መገዛት ይኖርባቸዋል።

መዝሙሩን ከራስ ህይወት ጋር በማገናኘት እራስን መመርመር ያስፈልጋል፦ መዝሙር የሚዘመረው ለአድማጩ ብቻ አይደለም። ንስሐ ግቡ እያለ የሚዘምር አንድ ዘማሪ ለራሱ ንስሐ የሚገባ መሆን ይጠበቅበታል።

═══◉ ❖ ◉═══

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

ወለወላዲቱ ድንግል

ወለመስቀሉ ክቡር አሜን!!!

═══◉ ❖ ◉═══